የሰ/መ/ቁ. 41385

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - ሰላማዊት አስደግድግ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ተረፈ ዘርጋው - ቀረበ

2. ፀጋዬ ደበበ - ቀረበ

3. ገመቹ ኡርጋ - ቀረበ

4. በቀለ መኰንን - አልቀረቡም

5. ዑመር መሐመድ - ቀረበ

6. ተስፋዬ ገረመው - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካች በሚያካሂደው የሕንፃ (ኮንስትራክሽን) ስራ በአናፂነት፣ በብረት ስራ እና በፌራዮ ስራ ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልጸው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጪ የስራ ውላቸው ስላቋረጠባቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በአገሪቱ ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች (ብረትና ሲሚንቶ) እጥረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ተጠሪዎችን ሲያሰናብት የጥሬ እቃው ሲገኝ ተመልሰው እንዲሰሩ በማስታወቂያ በመግለጽ እንደሆነም በመልሱ ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስንብቱ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት የሚደገፍ እንደሆነ ገልጾ መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ ስንብት በመሆኑ እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪዎች የጠየቁትን ክፍያ በሙሉ እንዲያገኙ ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት የቀረቡት አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና ስድስተኛ ተጠሪዎች በተገኙበት ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አራተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ እነሱ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተገለጸው አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ስራ ተጠናቆአል በሚል ሳይሆን፣ለህንፃው ስራ አስፈላጊ የሆኑት የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ይህ በመሆኑም የግንባታ እቃዎቹ ተሟልተው ሲገኙ ተጠሪዎች ተመልሰው ሊሰሩ እንደሚችሉ በማስታወቂያ የገለጸላቸው ስለመሆኑ ተመልክቶአል፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የግራ ቀኝ ወገኖች ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን፣ምስክሮቹ በሰጡት ቃልም በእርግጥ የተባሉት የግንባታ እቃዎች እጥረት ስለማጋጠሙ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ይህን መሰል ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ አሰሪ ሰራተኞችን ቢያሰናብት እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚባልበት አግባብ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አምልካች የስንብት እርምጃ የወሰደው ከህንፃው ስራ ጠባይ በመነሳት የተወሰኑ ስራዎች ተጠናቅቀዋል በሚል አይደለም፡፡ ይህም ሆኖ ግን የህንፃውን ስራ ለማስቀጠል የማይችልበት ደረጃ ላይ ስለመገኘቱ አልተካደም (አላከራከረም)፡፡ በመሆኑም ስንብቱ በአዋጁ አንቀጽ 30 በተመለተው ድንጋጌ የሚሸፈን ነው የሚለው የአመልካቹ ክርክር መቀበል የሚቻል ባይሆንም፣ስራው በእርግጥ የለም(ቆሞአል) እየተባለ አመልካች የስንብቱን እርምጃ መውሰድ አልነበረበትም? የሚለው በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ግን ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በአሰሪ አነሳሽነት ስለሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ በሚመለከት በአዋጁ ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ አሰሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውሉን የሚያቋርጥባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 28 የተቀመጡ ሲሆን፣ከእነዚህም ውስጥ ከድርጅቱ ድርጅትዊ አቋም ወይም የስራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የተቀመጠ ንኡስ አንቀጽ /2/ ይጠቀሳል፡፡ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘላቂታው የሚያስቆም የሰራተኞች ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት አሰሪው በማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል (ሁኔታው የስራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ተደርጎ እንደሚወሰድ) በተጠቀሰው ንኡስ አንቀጽ/2/ /ሀ/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች እጥረት የተነሣ የጀመረው የህንፃ ስራ ማስቀጠል አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአናፂነት፣በብረት እና በፌራዮ ስራ ቀጥሮ ሲያሰራቸው የነበሩትን ተጠሪዎችን ይዞ የሚጓዝበት ሁኔታ የለም ማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም ያለውን ብቸኛ አማራጭ ማለትም የስራ ውሉን የማቋረጥ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ እርምጃውን መውሰድ ያለበት ግን በሕጉ የተቀመጠውን ግልጽ ስርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሥርአቱ አስቀድሞ ማስጠንቀቅያ መስጠት ሲሆን፣አመልካች ግን ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ አልሰጠም፡፡ ስለዚህም አመልካች የስራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ ቢሆንም፣ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የተነሣ ሊኖርበት ከሚገባ ሐላፊነት ግን የሚድን አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት ከነበረበት የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ የስራ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሚለው የስር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ ግን ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39571 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70771 ኅዳር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረው የሥራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ እንዲከፍል የተወሰነበት ገንዘብ ይክፈል፡፡ ሌሎቹን ክፍያዎች ግን አይከፍልም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ